አሐዱ ባንክ
Ahadu Bank
ከብዙዎች ለብዙዎች
Inclusive Intermediation
ahadubank.com

አዲስ ቻምበር
ADDIS CHAMBER

ይቻላል
It's Possible!

ፀሐይ ኢንሹራንስ አ.ማ.
Tsehay Insurance S.C.
ፀሐይ ለሁሉም ታበራለች!!
The Sun Shines For All !!
ቦሌ ድልድይ ከብራስ ሆስፒታል ፊትለፊት
Bole Bridge, in front of Brass Hospital
Tel.+251 111 11 97 70/71 +251 111 11 98 27/97 93
Fax: +251 111 11 98 86
Website: www.tsehayinsurance.com
E-mail: marketingd@tsehayinsurance.com

# ንግድና ልማት

መስከረም 2016 50ኛ ዓመት እትም ☎ 011-5573544 ✉ 2458 E-mail: info@addischamber.com www.addischamber.com

## ጥራት ያለው የሙያና ቴክኒክ ስልጠና ተግባራዊ በማድረግ የስራ አጥ ቁጥርን መቀነስ እንደሚገባ ተነገረ

**በአሸናፊ ምትኩ**

ከ1994 ኢ.ም ጀምሮ በኢትዮጵያ ተግባራዊ መሆን የጀመረው የሙያና ቴክኒክ ስልጠና በርካቶችን የሙያ ባለቤት ያደረገና በተለይም ወጣቶች የስራ ፈጠራ ክህሎትን እንዲያዳብሩ በር የከፈተ ነው:: ይህ የስልጠና ፕሮግራም መሰጠት ከጀመረ አንስቶ በኢትዮጵያ እያደገ የመጣውን ኢንቨስትመንት የስራ ፍላጎትን በሚሟላት ረገድ የበኩሉን ሚና መጫወቱ ይነገራል::

ነገር ግን የሙያና ቴክኒክ ስልጠና በተፈለገው ልክ ወጣቶች ስራ ፈጣሪ እንዲሆኑ አላስቻለም የሚሉ ምልከታዎች በርካታ ናቸው:: ይህም ብቻ አይደለም በኢትዮጵያ የምርት ጥራት ከፍ እንዲልና ተወዳዳሪነት እንዲጨምር የሙያና ቴክኒክ ስልጠና ማእከላት የነበራቸው ሚና ብዙም አይደለም የሚሉ ጥናቶች ብቅ ማለት ጀምረዋል::

የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ከዴንማርክ ኮንፌደሬሽን ጋር በጋራ በቀረጹት ፕሮጀክት አማካኝነት የሙያና ስልጠና ተቋማት ብቃት ያላቸውን ሰልጣኞች እንዲያፈሩ እና የግሉ ዘርፍ የሚያስፈልገውን በሙያና ክህሎት የዳበረ ዜጋ እንዲያገኝ ምክር ቤቱ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል:: የዚህ አንድ አካል የሆነው የውይይት መድረክ በአዲስ አበባ ተካሂዳል:: የኢንዱስትሪዎች ምልከታ በሙያና ቴክኒክ ስልጠና በሚል መሪ ቃል የተካሄደው የውይይት መድረክ በርካታ ባለ ድርሻ አካላትን ያሳተፈ ሲሆን የጥናት ወረቀቶች እና ልምዶች የቀረቡበት መድረክ ነው::

ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## ምክር ቤቱ በውል ግብርና (Contract Farming) ምንነት እና ጠቀሜታ ዙርያ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ አካሄደ

**በስታፍ ሪፖርተር**

የአዲስ አበባ ንግድ እና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የግብርና ምርትን በተለይ ፍራፍሬ እና አትክልት አምራቾች እና አቀነባባሪዎች ላይ ትኩረት በማድረግ በውል ግብርና አሰራር እና ጠቀሜታ ላይ ትኩረት ያደረገ የውይይት መድረክ አካሂዷል::

በመድረኩ የግብርና ምርቶችን በመጠቀም በማቀነባበር ዘርፍ የተሰማሩ ድርጅቶች ተወካዮች ጥሪ የተደረገላቸው ባለድርሻዎች ተሳትፈዋል ::

ወደ ገጽ 3 ዞሯል

## PRESS
## አዲስ ቻምበር በኢግዚቢሽን ማእከል ላይ የነበረውን የማኔጅመንት ውል ስለመቋረጡ እና ማእከሉን በጋራ ለማልማት የቀረበለትን ጥሪ አስመልክቶ የተሰጠ ጋዜጣዊ መግለጫ

አዲስ ቻምበር
ADDIS CHAMBER

"ንግድ ምክር ቤታችን ከ1998 ኢ.ም ጀምሮ የኢግዚቢሽን ማእከልና እና የገበያ ልማት ድርጅትን በየጊዜው እየታደሰ በነበረው ውል አማካኝነት የማእከሉን የውስጥ አሰራር በአዲስ መልክ በማደራጀትና በማዋቀር ተቋማዊ አሰራሮቹን በማጠናከር ዘመናዊ የእቅድና የሪፖርት ፤የሰው ሀይል፤ የፋይናንስ፤የአስተዳደር፤የግዢ የሰው ሀይል፤ የኦዲትና ሌሎች ሥርአቶችን እንዲዘረጉና ተግባራዊ እንዲሆኑ በማድረግ ላለፉት 17 አመታት ሲያስተዳድረው ቆይቷል::

ይሁን እንጂ ጳጉሜ 2 2015 ኢ.ም በከተማው አስተዳደር በተሰየመው የማእከሉ የስራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢ አማካኝነት በተጻፈ ድብዳቤ ይህ ማእከሉን የማስተዳደር ውል ከጥቅምት 1 ቀን 2016 ኢ.ም ጀምሮ እንደሚቋረጥ በመግለጽ ከተማውን የሚመጥን የኢግዚቢሽንና ኮንቬንሽን ማእከል በጋራ ለመገንባት ምክር ቤታችን ጥሪ ቀርቦለታል:: አስከትሎም ከውሉ መቋረጥና በአዲስ መልክ ሊገነባ በታሰበው ግንባታ ዙርያ ዝርዝር ማብራሪያዎችን ሰብሳቢው ለሚዲያ መግለጫ ሰጥተዋል:: የዚህም ጋዜጣዊ መግለጫ ዋና አላማ በሚዲያ ለተሰራጩትና ተገቢነት በሌላቸው መረጃዎች ላይ በተነሱት ነጥቦች መልስ ለመስጠት ነው::

አዲስ ቻምበር ከተመሰረተበት ከ1939 ኢ.ም ጀምሮ ለሚወክለው የንግዱ ማህበረሰብ ልዩ ልዩ አገልግሎቶችን ሲሰጥ የቆየ ተቋም ሲሆን ኢግዚቢሽኖችን በአገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ሁኔታዎችና ወቅቱ በፈቀደለት መጠን አዘጋጅቶ በማካሄድ አገልግሎቱን ሲያቀርብ የቆየ ፋና ወጊና የዳበረ ልምድ ያለው ተቋም ነው::

በዚህ ረገድ ማእከሉን ለማስተዳደር የተደረገውን የማኔጅመነት ውል ባለመገንዘብ ምክር ቤታችን ካለው የአስተዳዳሪነት ሚና ባለፈ መዋእለ ንዋይ በማፍሰስ ማእከሉን በራሱ ለማልማት እንደነበረበት ተደርጎ የተሰተው የጋዜጣ ዘገባም ሆነ መግለጫ መታረም ያለበት ነው::

ምክር ቤታችን በፈረመው የማኔጅመንት ውል ላይ በሚጠበቅበት እና በተጣለበት ሀላፊነቱ መጠን ማእከሉን ተረክቦ በቀልጣፋና በትርፋማ የአስተዳደር ስልት በተገቢ ቁጥጥር ሆኖም አዋኪ ባልሆነ የማኔጅመንት ነጻነት ሲያስተዳድረው ቆይቷል:: ይሁን እንጂ ማእከሉ በማይንቀሳቀሱ ውቅሮች የተገነቡ የአዳራሾች ስብስብ እና ለኪራይ አላማ ከማያልፍ ተግባራት የማይውል ግኡዝ አካል ተደርጎ የተሳሳተ ግንዛቤ ቢወሰድበትም ምክር ቤታችን በተጣለበት የማኔጅመንት ሀላፊነቱ ማእከሉን የተሟላ ህጋዊ ሰውነት ያለው፤ራሱን የቻለ፤በተዘረጋለት ስርአት ፤በተደራጀበት መዋቅር እና በተቋማዊው አሰራሩ ፤ህልውናውን ጠብቆ በአስተማማኝ ቁመና ውጤታማ አገልግሎት መስጠት የቻለና እየሰጠ ያለ እንዲሆን ማድረጉን ማረጋገጥ እንፈልጋለን:: ከዚህ በተጻራሪ የተሰጠው የሚዲያ መግለጫ መሰረተ ቢስና በፍጹም ተቀባይነት የሌለው ነው::

መታወቅ ያለበት ጉዳይ በከተማ አስተዳድሩና በምክር ቤታችን መካከል በተገባው ስምምነት መሰረት የከተማ አስተዳድሩ ባለፉት 17 አመታት ውስጥ ካለምንም ወጪ የትርፍ ተካፋይ ሆኖ መቆየቱና ምክር ቤታችንን ጨምሮ ማናቸውም የማእከሉ ደንበኞች በሚፈፅሙት ክፍያዎች በሚያገኙት አገልግሎቶች በየጊዜው ባሳደገው ትርፋማነቱ የላቀ ጥቅምና የትርፍ ባለ ድርሻ ቢያደርገውም ምክር ቤታችን በውሉ እና በህግ የተጠበቀለትን ህጋዊ የትርፍ ክፍፍል የማግኘት መብቱ አለአግባብ እንደሆነ ተደርጎ በአደባባይ መነገሩ የትብብርና የአጋርነት ውሉን በአግባቡ ካለመረዳት የመነጨ ታላቅ ስህተት ነው::

ምክር ቤታችን በህግ አግባብ በስሙ ተመርቶ ፤ባለይዞታነቱ ተረጋግጦ ፤በይዞታው ላይ ያሉትን መሰረተ ልማቶች አብዛኛውን በራሱ ቀሪዎቹን በልማት አጋሮቹ ተሳትፎና ትብብር ገንብቶ ማእከሉን በማቋቋም ለሚወክላቸው አባላቱና የንግዱ ማህበረሰብ ምርቶቻቸውንና አ ገ ል ግ ሎ ቶ ቻ ቸ ው ን የሚያስተዋውቁበት አውደ ርእይ ማሳያና የገበያ ልማት ተግባራቶች ሲከናወንበት የቆየ ስፍራ ነው::

ማእከሉ ከምስረታው ጀምሮ የመንግስትና የግሉ ዘርፍ ትብብር እና ለጋራ አላማ አብሮ የመስራት ቤተ ሙከራ፤የዘላቂ ሽርክና ተምሳሌት ፤የግንኙነት እና የትስስር መድረክ ሆኖ ቆይቷል:: የከተማው አስተዳደር ከምክር ቤታችን ጋር በማእከሉ የማኔጅመንት ውል የፈጠረውን የትስስር ቋጠሮ ማእከሉን በጋራ እንድናለማው ያቀረበልንን ጥሪ በመላው የምክር ቤታችን አባላትና በንግዱ ማህበረሰብ ስም መቀበላችንን ስናረጋግጥ በቀጣይም በቂ ምክክር ተደርጎበትና ይልቁንም ለጋራ ጠቀሜታና ለከተማችን ልማት ዘላቂ ፋይዳ ያለው መሆኑን በማሳመን በምንፈጥረው ንቅናቄ ተፈጻሚ እንደምናደርግ ለሁሉም ባለ ድርሻ አካላት ለማሳወቅ እንወዳለን"

አዲስ ቻምበር
ADDIS CHAMBER

**በአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት እየተዘጋጀ የሚወጣ ጋዜጣ**

**፭0ኛ ዓመት እትም**

**ADDIS BUSINESS**

**ዋና አዘጋጅ**
አሸናፊ ምትኩ

**ዲዛይነር**
-

**ዐምደኞች**
ይድነቃቸው አለማየሁ
አሸናፊ ምትኩ
ሰናይት እሸቱ
ከፍያለው ዋሲሁን
ካሳሁን ማሞ

**የኤዲቶሪያል አባላት**
ዘካሪያስ አሰፋ-ሰብሳቢ
ሲሳይ ታደሰ- አባል
ካሳሁን ማሞ- አባል
አሸናፊ ምትኩ- አባል
ስዩም ጫኔ -አባል

**በአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት እየተዘጋጀ የሚወጣ ጋዜጣ 50ኛ ዓመት እትም**

**ADDIS BUSINESS**
መስከረም 2016 እትም

# ርዕሰ አንቀጽ

## የግሉና የመንግስት ትብብር መርህ በተግባር ይታይ!!

ምንም እንኳን የመንግስትና የግሉ ዘርፍ አጋርነት/ ትብብር (PPP) ትርጉሙ ሰፊና በተለያየ መንገድ የሚታይ ቢሆንም በአጭሩ ይህ ትብብር በሁለቱ ወገኖች መካከል የሚኖር የኮንትራት ትስስርና ማዕቀፍ ሊሆን ይችላል።

በመንግስትና በግሉ ዘርፍ መካከል በረጅም ጊዜ አብሮነት ለአንድ ዓላማ መስራት፣ ህዝባዊ አገልግሎትን ለመስጠት ያለመና ሁለቱም ወገኖች የሚጋሩትና በየራሳቸው የሚወስዱት ስጋትን (risk) ያካተተ ሲሆን በአብዛኛው የግሉም ዘርፍ የፋይናንስ ፍላጎት የሚታከልበት መሆኑ ትብብሩን የጋራ ያደርገዋል።

እነዚህን የጋራ የሚያደርጋቸዉ ዓቢይ ጉዳይ የመንግስትና የግሉ ዘርፍ ተጣማሪዎች የተለያየ ፍላጎት ማለትም የግሉ ዘርፍን አገልግሎት በመስጠት የተወሰነ ትርፍ የማግኘት ፍላጎትና የመንግስትን የአገልግሎት ፍትሀዊ ተደራሽነት ማረጋገጥ ፍላጎት (welfare) በማቻቻል ሁለቱም ወገኖች እንዴት ተጠቃሚ መሆን የሚለው ጉዳይ ነው።

የመንግስትና የግሉ ዘርፍ አጋርነት/ትብብር በራሱ ልዩ የሆኑ ባህሪያት ያሉት ሲሆን የመንግስትና የግሉ ዘርፍ ተዋንያን ድርሻ፣ ተሳትፎና ስጋት ለየቅል መሆኑ አንዱ የባህሪዉ መገለጫ ነው።
ስጋትን ከመንግስት ወደ ግል ዘርፍ በመጠኑ ማሸጋገር በሁሉም የትብብር ማዕቀፎች የሚታይ ጉዳይ ሆኖ ዋነኛ ዓላማው ግን ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረዉ ይህ አይነት ትብብር/አጋርነት የሁለቱን ወገኖች ፍላጎት በማቻቻል ለጋራ ተጠቃሚነት ማዋል ነው።

የተለያዩ የመንግስትና የግሉ ዘርፍ ጥምረትና አጋርነት ተሞክሮዎችና ማዕቀፎች እንደሚያሳዩት ሁለቱም ወገኖች ሊጋሩት የሚችሉት በርካታ የሃላፊነትና የስጋት አይነቶች እንዲሁም የአካሄድ አማራጮች/ሞዴሎች አሉ። የአጋርነት ሞዴል አማራጮች ትንሽ ከሚባለው ስራን (አስተዳደርን) ለውጭ አካል በኮንትራት ሰጥቶ ከማሰራት እስከ ከፍተኛዉ ወደ ግል ይዞታ ማዞርና ማጋራት ይደርሳል።

እያንዳንዱ የአጋርነት ምርጫ አካሄድ የራሱ የሆነ ጥቅምና ጉዳት ያለው ሲሆን በተለያዩ ደረጃና መጠን የመንግስትና የግሉ ዘርፍ አጋርነትን ዓላማ ሊያሳካ የሚችል መሆኑን ማየት ይቻላል።
ውጤታማ የግሉ ዘርፍና የመንግስት አጋርነት ማእቀፍ ለመምረጥ የተለያዩ የኢኮኖሚ እና ማህበራዊ ጉዳዮችን መዳሰስ ተገቢ ሲሆን የመንግስትና የግሉ ዘርፍ አጋርነት ሁልጊዜም እንደ ብቸኛ እና ዋናው አማራጭ የማይታይ ይልቁንም በተጨባጭ ሁኔታ ላይ የተመረኮዘ ነው።

አጋርነት በግብ፣ በአካሄድና ቅርጽ ፣ በሂደትና በሁለቱ ወገኖች ተጨባጭ ሁኔታ የሚለያይ ነው።ከሁሉም በላይ ስኬታማ አካሄዶችን ለመተግበር እንደ ሁኔታው የሚለዋወጥና በአትራፊነት አካሄድ የተቃኘ አሰራር መከተል መልካም መሆኑን ከሌሎች ሀገራት ምርጥ ተሞክሮ ማየት መቻል አለብን።

የመንግስትና የግሉ ዘርፍ ጥምረት በኢትዮጵያ ከተሞች በተለይም በአዲስ አበባ በዋናነት የሚፈለግበት ምክንያት በመንግስት ረገድ ሊቀርብ የሚገባዉን የመሰረተ ልማት አቅርቦትንና የህብረተሰቡን ወቅታዊና አንገብጋቢ ፍላጎቶች ለማጣጣም እና ብቁ የሆነ አሰራርን መዘርጋት ነዉ።

ምንም እንኳን ሀገሪቱ የጥምረትን አስፈላጊነት በልማት ፖሊሲዎችና ስትራተጂዎች ያካተተች ቢሆንም ለስኬታማ አፈጻጸም የሚረዱና መሬት የወረዱ ዝርዝር ፖሊሲዎች ፣ ህጋዊ ማዕቀፎች፣ ተቋማዊ አደረጃጀቶችና የአሰራር ስርዓቶች ተቀርጸው ወደ ስራ መግባት አለባቸው።

የግሉ ዘርፍ ሀብት እና ዕዉቀት በመሰረተ ልማትና አገልግሎቶች አቅርቦቶች ረገድ ያለዉን ክፍተት ለመሙላት ወሳኝ ሚና አለዉ። ይህን ከግንዛቤ ዉስጥ በመክተት የተለያዩ መሰረተ ልማቶችን እና አገልግሎቶችን በመንግስትና የግሉ ዘርፍ ትብብር/ ጥምረት (PPP) ማልማትን በተመለከተ የግሉ ዘርፍና የመንግስት አመለካከት በብዙ አቅጣጫዎች ሊታይ ይገባል ። የግሉና የመንግስት ትብብር መርህ በከተማችንም ሆነ በሀገራችን በተግባር ይታይ!!

TEL. 011-5518055 | 011-5519713
011-5155221
Fax. 011-5511479 P.O.BoX. 2458

# የውል ግብርና እድሎችና ተግዳሮቶች በኢትዮጵያ



**በአሸናፊ ምትኩ**

እንደ አለምአቀፉ የምግብና እርሻ ድርጅት ሪፖርት የአለም የምግብ ስርአት እንዲዘምንና የምግብ ተደራሽነት እንዲጨምር አነስተኛ ገበሬዎችን በተለያዩ ሁኔታዎች መደገፍና አቅማቸውን ማሳደግ እንደሚገባ ጠቁማል:: ለዚህ ቁልፍ መሳሪያ ተብሎ የተነሳው ጉዳይ ደግሞ የውል ግብርና ወይም ( contract farming) ነው:: የውል ግብርና በአለማችን እያደገ የመጣ የግብርና ቢዝነስ ሞዴል ነው::

በተለይም ይህ የግብርና ስርአት ባለሀብቶችንና አርሶአደሮችን በውል ወይም በስምምነት የሚያስተሳስር ሲሆን ይህ ስምምነት አንዱ በገንዘብ ሌላው ደግሞ በእርሻ መሬቱ አማካኝነት የጋራ ጥምረት በመፍጠር የተሻለ የግብርና ምርት እንዲያገኙ ያስችላል:: በአብዛኛው በማደግ ላይ ባሉ ሀገራት ባህላዊ ግብርና ዘዴ (subsistence agriculture) በስፋት ይስተዋላል:: በዚህም ተነሳ ታዲያ አርሶ አደሮች የሚያመርቱት ምርት ከእጅ ወደ አፍ ይሆንና ከተመረተው ምርት ለገበያ የሚቀርበው አነስተኛ እንደሆነ የአለም የምግብና እርሻ ድርጅት መረጃዎች የሚያሳዩት::

ለዚህም በዋናነት የተቀመጠው ምክንያት አነስተኛ አርሶ አደሮች ዘመናዊ የአስተራረስ ዘዴን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል አቅም እውቀትና ክህሎት አለመኖሩ ነው ይላል:: ስለሆነም እንዲህ አይነት ተግዳሮቶችን ለመፍታት የውል ግብርና አይነተኛ ሚናን ይጫወታል የሚል እምነት አለው ድርጅቱ::

በከፍተኛ ደረጃ እያደገ የመጣውን የሰው ልጆች የምግብ ፍላጎት ለማዳረስ አለም ላይ ያለውን የግብርና ስርአት (Agricultural system) ማዘመን ለድርድር የሚቀርብ ጉዳይ አይደለም:: የህዝብ ቁጥር መጨመር እና የከተሜነት መስፋፋት፣ የሚታረስ መሬት መጠን እየቀነሰ መሄዱ ፣ሀገራዊና አለም አቀፋዊ የፖለቲካ ግጭቶች መስፋፋት እና የአለም የሙቀት መጠን መጨመር እያስከተለ ያለው ድርቅ የሰው ልጆች የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የሚደርገወን ጥረት ፈታኝ አድርገውታል:: በመሆኑም እንዲህ አይነት በግብርና ዘርፍ ላይ የሚጋጥሙ ችግሮችን ለማቃለል የግሉ ዘርፍና አርሶ አደሮች በጋራ ወይም በውል የሚሰሩበት አሰራር መፍጠር ወሳኝ ነው:: ለዚህም ነው የውል ግብርና አስፈላጊነት በብዙዎች ዘንድ እየታመነበት የመጣው::

የውል ግብርና ረዘም ላሉ አመታት በበርካታ ሀገራት በለተይም ባደጉት ሀገራት እየተለመደ የመጣ አሰራር ሲሆን አሁን ደግሞ የውል ግብርና በማደግ ላይ ባሉ ሀገራት በተለይም እንደ ኢትዮጵያ በመሳሰሉ ሀገራት በስፋት እየተለመደ የመጣ የግብርና ዘዴ ነው:: ይህ የግብርና አሰራር በኢትዮጵያ ከረጅም አመታት ጀምሮ በአርሶአደሩ ማህበረሰብ ሲከናወን የቆየ መሆኑን በቅርቡ በተደረገ አውደ ጥናት ላይ ተገልጿል:: በአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ሰሞኑን በተዘጋጀው እና የውል ግብርና ላይ ትኩረቱን ባደረገው የውይይት መድረክ ላይ በርካታ የንግዱ ማህበረሰብ አባላትና ባለ ድርሻ አካላት ተሳታፊ በመሆን በውል ግብርና ዙርያ ስላሉ መልካም እድሎች እና የህግ ማእቀፎች ዙርያ ሰፋ ያለ ውይይት አካሄደዋል:: የኢትዮጵያ የግብርና አሰራር አሁንም ከባህላዊ አስተራረስ አልተላቀቀም ያሉት በእለቱ የጥናት ወረቀት ያቀረቡትና የግብርና ምጣኔሀብት ተመራማሪ በየነ ታደሰ( ዶ/ር) ናቸው:: ስለሆነም የተሻለ ግብርና ምርት ለማግኘት የውል ግብርናን በስፋት ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል ብለዋል::

የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ከዴንማርክ ኮንፌደሬሽን ጋር በቀረጸው ፕሮጀክት አማካኝነት የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ እንዲሻሻልና የተሻለ ምርትና ገበያ እንዲፈጠር በመስራት ላይ ይገኛል:: የዚህ አንዱ አካል የሆነው የውይይት መድረክ ላይ የጥናት ወረቀት ያቀረቡት በየነ ታደሰ( ዶ/ር) የውል ግብርና በኢትዮጵያ በተደራጀ መልኩ እያደገ እንደመጣ የገለጹ ሲሆን ነገር ግን የግሉ ዘርፍ ተሳትፎና በውል እርሻ ዙርያ ያለው ግንዛቤ አሁንም አነስተኛ እንደሆነ ተናግረዋል:: ምንም እንኳን ለውል ግብርና የሚሆን ሰፊ እድል ቢኖርም በውል ግብርና ለሚሳተፉ ዜጎች የሚሆን በቂ የፋይናንስ አቅርቦትና ብድር አለመኖርና በውል ግብርና ላይ ያለው ግንዛቤ አነስተኛ መሆን ይህ የግብርና ዘዴ እንዳይስፋፋ ማነቆ እንደሆነ ገልጸዋል:: ይህም ብቻ አይደለም የውል ግብርና በታለመለት መልኩ ተግባራዊ እንዳይሆን በርካታ ተግዳሮቶች እንዳሉ የገለጹ ሲሆን ከነዚህም መካከል በግብርና ምርቶች ላይ የሚስተዋለው የዋጋ አለመረጋጋት ለውል ግብርና ተዋንያን ፈታኝ ሆኖ እንደሚቀጥል ተመራማሪው ገልጸዋል:: የውል ግብርና አሁንም ተግዳሮቶች ቢኖሩበትም በርካታ ባለሀብቶችና ኩባንያዎች ይህን ውል በመጠቀም ከአርሶ አደሮች ጋር በጋራ በመስራት ጥራት ያለው የግብርና ምርት ማምረት እንደቻሉ ተመራማሪው ገልጸዋል::

በተለይም በግብርና ማቀነባበር ላይ የተሰማሩ ኩባንያዎች ለሚያመርቱት ምርት የሚሆን የግብርና ሰብል /ምርት በጥራትና በብዛት ማግኘት እንደቻሉ ተመራማሪው ተናግረዋል:: ሆኖም ግን በዚህ የውል ግብርና በርካታ ተግዳሮቶችም የተስተዋሉበት እንደሆነ የጥናታቸውን ውጤት ዋቢ በማድረግ ተመራማሪው ገልጸዋል:: ለአብነትም ያክል አርሶ አደሮች በውል ግብርና ላይ ያላቸው ግንዛቤ አነስተኛ መሆን ፣የውል ግብርና ህጎችን በአግባቡ አለመረዳትና አለመተግበር ለአብነትም ያክል ምርት ከተሰበሰበ በኋላ በውሉ መሰረት ምርቱን ለመሸጥ ፈቃደኛ አለመሆን ፣የምርት ጥራት መጓደል፣ የመሳሰሉት እንደ ዋና ዋና ተግዳሮቶች መሆናቸውን አነስተዋል ተመራማሪው::

በዚህ የውይይት መድረክ ላይ ከግብርና ሚኒስቴር የመጡ ከፍተኛ ባለሙያ በኢትዮጵያ ስላለው የውል ግብርና ሁኔታ የህግ ማአቀፎች እና አሰራሮች ሰፋ ያለ ማብራሪያ ሰጥተዋል:: ባለሙያው አቶ ሱልጣን መሀመድ የግብርና ውል በአውሮጳ ዋናው የግብርና ምርት አቅርቦት መገኛ መሆኑን ተናግረዋል:: ከዚህም ባለፈ ባለሙያው የውል ግብርና ለአርሶ አደሮች በርካታ ጥቅሞች እንዳሉት የተናገሩ ሲሆን አርሶ አደሮች በዚህ ውል አማካኝነት የማምረት አቅማቸው እንደሚያድግና የገበያ ተደራሽነታቸው እንደሚስፋፋ ተናግረዋል::

በባለሀብቶችና በአርሶ አደሮች መካከል የሚደረገው የውል ግብርና የአርሶ አደሮችን የማምረት አቅም ከማሳደግ ባለፈም ባለሀብቶች ማህበራዊ ሀላፊነታቸውን እንዲወጡ በር ከፋች ነው ብለዋል ባለሙያው:: ለአብነትም ያክል በውል ግብርና የተሰማሩ ባለሀብቶች ሙዋለ ንዋይ ባፈሰሱባቸው አከባቢዎች እንደ መንገድ፣ ውሀና የህክምና ማእከሎችን ለነዋሪው በመገንባት ያላቸው ሚና ከፍተኛ እንደሆነ ተናግረዋል::

በውል ግብርና ዙርያ በተደረገው የውይይት መድረክ ላይ የግሉን ዘርፍ በመወከል የተገኙ ተሳታፊዎች ሀሳባቸውን ሰንዝረዋል:: ከተነሱት ሀሳቦችና አስተያየቶች መካከል በውል ግብርና ዙርያ ያለው መረጃ አነስተኛ መሆን እና ይህን ለመቀየር ሰፊ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራን መስራት፣ በውል ግብርና ዙርያ የወጡ አዋጆችን በስፋት ማስተዋወቅ እና በአግባቡ እንዲተገበሩ ማድረግ፣ የውል ግብርና ፖሊሲን ማዘጋጀትና መተግበር ለስራ ፈጠራ ያላቸውን ሚና ማጎልበት የሚሉት ይገኙበታል::

ከዚህም ባለፈ የውል ግብርና በመስኖ ሊለሙ የሚችሉ አከባቢዎችን ከግምት ውስጥ እንዲያስገባና ተጨማሪ ምርት እና የስራ እድል እንዲፈጥር ሀሳብ ተነስቷል::
ውድ አንባቢያን በዚህ ርእሰ ጉዳይ ዙርያ ተጨማሪ መረጃዎችን ይዘን እንመለሳለን::

## ሚስተር ክላቨር ጋቴቴ የተባበሩት መንግስታት ኢኮኖሚክ ኮሚሽን ዋና ስራ አስፈጻሚ ሆነው ተሾሙ



የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ጸሀፊ አንቶኒዮ ጉቴሬዝ የሩዋንዳውን ሚስተር ክላቨር ጋቴቴ የአፈሪቃ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን ዋና ስራ አስፈጻሚ አድርገው መሾማቸውን አስታውቀዋል:: አንቶኒዮ ጉቴሬዝ ለቀድሞው የድርጅቱ ዋና ጸሀፊ ቬራ ሶንግዌ እንዲሁም ለምክትላቸው አንቶንዮ ፔድሮ አድናቆታቸውን ቸረዋል::

አዲሱ ተሻሚ በአሁኑ ወቅት በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሩዋንዳ አምባሳደርና ተጠሪ በመሆን በኒውዮርክ የሚገኙ ሲሆን በሙያቸው እውቅ የምጣኔሀብት ባለሙያና የስትራቴጂ አመራር ባለሙያ ናቸው:: ሚስተር ጋቴቴ በሀገራቸው ሩዋንዳ የመሰረተ ልማት ሚኒስቴር ፣የፋይናንስና ፕላኒንግ ሚኔስቴር በመሆን አገልግለዋል:: ከዚህም በተጨማሪ የሩዋንዳ ብሄራዊ ባንክን ከምክትል እስከ ዋና ገዢ በመሆን አገልግለዋል:: ሚስተር ጋቴቴ የዲፕሎማሲ ስራቸው እ.አ.አ በ2005 የተጀመረ ሲሆን እስከ 2009 ድረስ በለንደን በመቆት በሃላም በዛው አመት በእንግሊዝ የሩዋንዳ አምባሳደር በመሆን አገልግለዋል::

ሚስተር ጋቴቴ በግብርና ምጣኔሀብት ካናዳ ከሚገኘው ብሪቲሽ ኮሎምቢያ ዩኒቨርሲቲ የሁለተኛ ዲግሪ አላቸው:: ሹመታቸውን ተከትሎ የዩኤን ኢሲኤ ተጠባባቂ ዋና ስራ አስፈጻሚ የሆኑት አንቶንዮ ፔድሮ የመልካም ምኞት መልእክታቸውን አስተላልፈዋል::

## አዲስ ቻምበር አለምአቀፉን የግብርና እና የምግብ አውደርእይ በአዲስ አበባ ሚሊኒየም ለማድረግ ዝግጅቱን እያጠናቀቀ እንደሆነ ተነገረ።

**አዲስ ቻምበር ( ጥቅምት 5 2016 አ.ም)፡-** አዲስ ቻምበር ለንግዱ ህብረተሰብ ከሚሰጣቸው አገልግሎቶች መካከል አለምአቀፍ የንግድ ትርኢቶችን ማዘጋጀት ሲሆን የንግድ ምክር ቤቱ ደረጃቸውን የጠበቁ አለምአቀፍ የንግድ አውደርዮችን በማዘጋጀት የንግድ ትስስር ፣የገበያ እድል እንዲሁም ንግድና ኢንቨስትመንት እንዲስፋፉ ጉልህ ድርሻ በማበርከት ላይ ይገኛል::

የንግድ ምክር ቤቱ ከሚያካሄዳቸው አውደርዮች መካከል የእርሻና የምግብ አውደርዮች ይገኙበታል:: በመጪው ህዳር ወር በአዲስ አበባ ሚሌንየም አዳራሽ የሚደረገው የእርሻና የምግብ አውደርእይ በግብርና ኢንዱስትር እሴትን መጨመርን እናሳድግ የሚል መሪ ቃልን ያነገበ ሲሆን የንግዱ ማህበረሰብ በጉጉት ከሚጠብቃቸው ሁነቶች መካከል ዋናው ነው::

ይህ የንግድ ትርኢት በየአመቱ በአዲስ ቻምበር የሚዘጋጅ ሲሆን በግብርና ማቀነባበር ስራ ላይ የተሰማሩ አምራቾችና የእርሻ ቴክኖሎጂ ባለቤቶችን በአንድ የሚያስተሳስር መድረክ እንደሚሆን ይጠበቃል:: ስለሆነም የንግዱ ማህበረሰብ በተለይም በእርሻና በምግብ ማቀነባበር የተሰማሩ ባለሀብቶች ይህን መልካም አጋጣሚ እንዲጠቀሙ ንግድ ምክር ቤቱ ጥሪውን አቅርባል::

## ጥራት ያለው የሙያና ቴክኒክ ስልጠና ተግባራዊ በማድረግ የስራ አጥ ቁጥርን መቀነስ እንደሚገባ ተነገረ

ከ ገጽ 1 የዞረ

በዚህ የውይይት መድረክ ላይ የስራ ክህሎት ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ንጉሱ ጥላሁን የተገኙ ሲሆን ጥራቱን የጠበቀ የሙያና ቴክኒክ ስልጠና በኢትዮጵያ እውን ማድረግ እስካልተቻለ ድረስ ገበያው የሚፈልገውን የሰለጠነ ሰው ሀይል ማግኘት እንደማይችል ገለጽዋል::
ምንም እንኳን በኢትዮጵያ የሙያና ቴክኒክ ስልጠና ማእከላት ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ ቢመጣም አሁንም ተግዳሮቶች አሉበት ያሉ ሲሆን ከነዚህም መካከል የማህበረሰቡ ለሙያና ስልጠና ተቋማት ያለው አመለካከለት ዝቅተኛ መሆን፤ ጥራቱን ያልጠበቀ ስልጠና፤ በኢንዱስትሪና በሙያና ቴክኒክ ማሰልጠኛ ተቋማት መካከል ያለው ግንኙነት ደካማ መሆን እና የኢንዱስትሪ ተቋማት በራቸውን ለሙያና ቴክኒክ ሰልጣኞች ክፍት አለማድረግ የሚሉት ይገኙበታል ብለዋል::
ከዚህም ባለፈ ጥራት ያለው የሙያና ቴክኒክ ስልጠናን በኢትዮጵያ ተግባራዊ ለማድረግ የመንግስት ጥረት ብቻ በቂ አይደለም ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው ይልቁንስ የግሉ ዘርፍ ከመንግስት ጎን በመሆን ውጤታማና የንግድና ኢንቨስትመንት ተወዳዳሪነትን እውን ሊያደርግ የሚችሉ የሙያና ቴክኒክ ስልጠና ማእከላትን ማፍራት እንዲቻል ጥሪ አቅርበዋል::
የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤትን በመወከል በወቅቱ ንግግር ያደረጉት የምክር ቤቱ ምክትል ዋና ጸሀፊ አቶ ዘካርያስ አሰፋ በበኩላቸው ንግድ ምክር ቤቱ በኢትዮጵያ ጠንካራና ተወዳዳሪ የግል ዘርፍ እንዲፈጠር እየሰራ እንደሆነ የተናገሩ ሲሆን የቴክኒክና ሙያ ስልጠና የግሉ ዘርፍ የሚፈልገውን የሰለጠነ የሰው ሀይል በመቅጠር ያለው ሚና ከፍተኛ ነው ያሉ ሲሆን መንግስት የሙያና ቴክኒክ ስልጠና ፖሊሲን በማዘጋጀት ያሳየውን ቁርጠኛነት አድንቀዋል:: ከዚህም ባለፈ የሙያና ቴክኒክ ስልጠናዎችን የኢንዱስትሪው ዘርፍ ከሚፈልገው ጋር አብሮ ማጣመር እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል::
በዚህ የውይይት መድረክ ላይ የሙያና ቴክኒክ ስልጠናን አስመልክቶ የጥናት ወረቀቶች የቀረቡ ሲሆን ከዴንማርር ኮንፌደሬሽን የተወከሉ ባለሙያ ልምዳቸውን አካፍለዋል:: የቴክኒክና ሙያ ስልጠና እራሱን የቻለ የኩባንያ አስተዳደር ወይም ገቨርናንስ እንደሚያስፈልጋቸው የተናገሩ ሲሆን የዴንማርር ኮንፌደሬሽን ከአዲስ ቻምበር ጋር በጋራ በመስራት በሙያና ቴክኒክ ስልጠና ዙርያ የሚታዩ ችግሮችን ለመፍታት ፕሮጀክት ቀርጸው እየሰሩ እንደሆነ ሚስ ሚሊሴንት ተናግረዋል::
በዚህ የውይይት መድረክ ላይ ከባለ ድርሻ አካላት በርካታ አስተያየቶችና ግብአቶች የተሰነዘሩ ሲሆን ከነዚህም መካከል በአዲስ ቻምበር የተዘጋጀው መድረክ የጋራ መድረኮችን ለመፍጠርና ባለ ድርሻ አካላትን በአንድ ላይ እንዲመክሩ ያለው ጠቀሜታ ጉልህ መሆኑን፤ በሙያና ቴክኒክ ስልጠና ዙርያ የተሰማሩ ባለ ድርሻ አካላት ራእይና ተልካቸውን ማዋሃድ የሚችሉበት መድረክ እንዲፈጠር ማድረግ፤ በግሉ ዘርፍና በመንግስት መካከል ያለውን የትብብር መድረክ ማጠናከር፤ ፍላጎትን መሰረት ያደረጉ ስልጠናዎች ላይ ትኩረት መስጠት፤ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቃማትን ፤ የፋይናንስ ተቃማትን በሙያና ቴክኒክ ስልጠና ፕሮግራሞች ላይ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማድረግ የሚሉት ይገኙበታል::

## ምክር ቤቱ በውል ግብርና (Contract Farming) ምንነት እና ጠቀሜታ ዙርያ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ አካሄደ





ከ ገጽ 1 የዞረ

የውል ግብርና በሃገራችን ቀደም ሲል የነበረ እና በዘመናዊ መልክ አለመከናወኑ አዲስ እንደሚያስመስለው የተናገሩት እና የውል ግብርና በሌሎች ሃገሮች እና በሃገራችን ያለውን ተሞክሮ ያቀረቡት በማማከር ዘርፍ የተሰማሩት ደ/ር በየነ ታደሰ የውል ግብርና በከፍተኛ ሁኔታ በሌሎች ሃገሮች የሚሰራበት እና ውጤታማ የሆነ አፈጻጸሙ የተለያዩ ሂደቶችን የሚያካትት መሆኑን አንስተዋል::

እንደባለሞያው በሃገራችን የውል ግብርና ተግባራዊ የሆነባቸው ዘርፎች መኖራቸውንም አንስተዋል :: በስኳር ፋብሪካዎች ፣በማር፣በገብስ እና በአቦካዶ ምርቶች ላይ ገበሬዎች ከአቀናባሪዎች ጋር በገቡት ውል የሚሰራባቸው መሆኑን ጠቅሰዋል::
 የውል ግብርና አሁን ላይ ግንዛቤውን በመጨመር የህግ ማእቀፍ በማዘጋጀት እና የመንግስት አመራር ታክሎበት ምርት እና ምርታማነትን ለመጨመር መተግበሩ ጥያቄ ውስጥ መግባት የሌለበት መሆኑንም አንስተዋል::

የውል ግብርና የገበያ ትስስር መፍጠር የሚያስችል በገበያ ማፈላለግ ሂደት የሚወጡ ወጭዎችን መቀነስ የሚያስችል ፤ በአነስተኛ ደረጃ ያሉ ገበሬዎችን የኢኮኖሚ ተጠቃሚ የሚያደርግ፤ ልምድ እና የእውቀት ሽግግር የሚፈጠርበት እንደሆነ ተብራርቷል::

የውል ግብርና ክንውንን በሃገራችን ያለውን የፖሊሲ እንዲሁም ተግዳሮቶቹን እስመልክቶ ማብራርያ የሰጡት በግብርና ሚኒስቴር የውል ግብርና ቡድን መሪ አቶ ሱልጣን መሃመድ የውል ግብርና በምርት ሂደት የሚያጋጥሙ፤ጥራትን፤መጠንን እና ከምርት አይነት ጋር ተያይዘው ለሚከሰቱ ችግሮች መፍትሄ መስጠት የሚያስችል መሆኑን ጠቁመዋል::
የውል ግብርና በሃገራችን በአዋጅ የተደገፈ እና በሌሎች ሃገሮች ተግባር ላይ የሚውሉ አሰራሮችን የሚከተል ነውም ብለዋል::

ባሳለፍነው 2014/15 ዓ.ም 772,857 ሄክታር መሬት በዚሁ በውል ግብርና አገልግሎት ላይ የዋለ ሲሆን በዚህም16,883,304 ኩንታል የምርት አይነት መገኘቱንም ገልጸዋል::

# በቀጣይ አስር አመታት 80 በመቶ የሚሆነውን የግንባታ ግብዓት በአገር ውስጥ ለማምረት መወጠኑን የከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር አስታወቀ

**በከፍያለው ዋሲሁን**

በከፍያለው ዋሲሁን
የከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር ሚንስትር ደኤታ ወንድሙ ሲታ(ኢ/ር) ኢትዮጵያ ለግንባታው ዘርፍ የሚያስፈልጋትን 60 በመቶ የሚሆነውን ግብዓት ከውጭ እያስገባች መሆኑን ተናግረዋል ፡፡ በግንባታው ዘርፍ ላይ ያተኮረውና ከሶስት አመታት መቋረጥ በኃላ የተካሄደው 17ተኛው ኢትዮ-ኮን ዓለም አቀፍ የኮንስትራክሽን ኢግዚቢሽን በርካታ የዘርፍ ተዋንያኖች የተሳተፉበት ነው፡፡ ለአራት ቀናት በተካሄደው የንግድ ትርዒት የኮንስትራክሽን ስራ ተቋራጮች ፣ የዘመኑ ቴክኖሎጂና የአሰራር ስርዓት የደረሰበትን ደረጃ በአንድ ስፍራ ለማየትና ለመረዳት ብሎም ግብይት ለመፍፀም በማለም የተካሄደ ነው፡፡

ባለፉት 20 ዓመታት በኢትዮጵያ የግንባታው ዘርፍ ኢንዱስትሪ ከፍተኛ እድገት አስመዝግቧል ያሉት ወንድሙ ሲታ በእነዚህ አመታት ዘርፉ ለጥቅል አመታዊ ምርት 300 ቢሊየን ብር ገደማ አስተዋፆ አበርክቶ እንደነበረው አውስተዋል፡፡ ዘርፉ የተለያዩ ችግሮች ቢኖሩበትም አሁን ላይ ለጥቅል አመታዊ ምርት 470 ቢሊየን ብር ገደማ ድጋፍ አድርጓል ፡፡

ከግብርናው ዘርፍ በመቀጠል ከፍተኛ የስራ ዕድል የፈጠረ ዘርፍ መሆኑን ጠቅሰው ለሀገር ኢኮኖሚ እድገት ከፍተኛ ሚና ማበርከቱን ቀጥሏል ብለዋል፡፡ አክለውም የኮንስትራክሽን ዘርፍ ላይ ያተኮረ ኢግዚቢሽን መዘጋጀቱ ምርቶች ለእይታ የሚቀርቡበት ፣ የግንባታ ቴክኖሎጅዎች የሚተዋወቁበት ከመሆኑም በላይ በዘርፉ የሚታዩ ችግሮች የሚፈቱበትና አዳዲስ ቴክኖሎጅዎች የሚተዋወቁበት መድረክ ነው ብለዋል ፡፡
እንደ አንድ የመንግስት አካልና በተለይም የግንባታውን ዘርፍ እንደሚመራ ተቋም ዘርፉ ለአገር ኢኮኖሚ መጫወት ያለበትን ሚና እንዲያበረክት ሚንስቴር መስሪያ ቤታቸው እየሰራ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

በዋነኝነት ለኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ችግር ሆኖ እየታየ ያለው የአገር ውስጥ ስራ ተቋራጮች ፣ ባለሙያዎች ፣ አማካሪዎች ፣ የተወዳዳሪነት ጉዳይ ነው ፡፡
ይህ ተወዳዳሪነት ደግሞ ሰለተመኘን ወይንም የዘርፉን ተዋንያን ቁጥር ስላበዛን ብቻ የሚመጣ አይደለም ብለዋል ፡፡ በመሆኑም በግንባታው ዘርፍ ላይ ያሉ ተዋንያኖች ለዘርፉ እድገት በሙሉ አቅማቸው በመስራት ተወዳዳሪ ለማድረግ መስራት እንዳለባቸው ያላቸውን እምነት ገልፀዋል ፡፡

የዚህን ኢንዱስትሪ ተወዳዳሪነት ለመገንባት ከሁሉም ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር እየሰራን እንገኛለን ብለዋል፡፡ አሁን ላይ በግንባታው ዘርፍ ላይ የሚታዩ ችግሮች መካከል አንዱ የኮንስትራክሽን ግብዓት እጥረት አንዱ ነው ያሉት ኢንጅነር ወንድሙ፤ ይህንን በአገር ውስጥ በማምረት የሀገሪቱን የውጭ ምንዛሬ ወጭን ለመቀነስ እየተሰራ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ኢትዮጵያ ለግንባታ ሊውል የሚችል ግብዓት ቢኖርም 60 በመቶ የሚሆነው የግንባታ ግብዓት ከውጭ አገር የሚገባ መሆኑን ተናግረዋል፡፡ ይህንን ግብዓት ወደ ግንባታ መቀየር ባለመቻሉ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ውጭ እያወጣን ነው ያሉት ኢንጅነር ወንድሙ፡፡

በሚቀጥሉት አስር ዓመታት በተለይ ዋና ዋና የሚባሉትን የኮንስትራክሽን ግብዓቶችን ቢያንስ 80 በመቶ የሚሆነውን በአገር ውስጥ ለማምረት ውጥን መያዙን ተናግረዋል ፡፡

አክለውም በግንባታው ዘርፍ የሚታየውን ችግር ለመፍታት የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ፖሊሲ ለመከለስ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ሚንስቴር መስሪያ ቤታቸው እየሰራ እንደሚገኝ ተናግረዋል፡፡ በዘርፉ ያለው ችግር ይህ ብቻ አይደለም ከቴክኖሎጂ አጠቃቀም ጋር ተያይዞ ችግሮርች አሉ ያሉት ኢንጅነር ወንድሙ በተለይ የአገር ውስጥ ስራ ተቋራጮች ከውጭ ከሚመጡ ተቋራጮች ጋር እንዳይወዳደሩ ያደረጋቸው አንዱ በቴክኖሎጅ ወደ ኃላ መቅረታቸው ነው ብለዋል ፡፡
በመሆኑም በግንባታ ኢንዱስትሪ ምርታማነት አሉታዊ ተፅዕኖ እያሳደረ መሆኑን ጠቅሰው ፤ ዘርፉን ለማሳደግ የቴክኖሎጂን አቅም ማሳደግ እንደሚያስፈልግ አምነን በግንባታ ዘርፍ ፖሊሲው ውስጥ እንዲካተት የተደረገ መሆኑን ገልፀዋል ፡፡

ዘርፉ ብዙ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች ያሉበት ፣ ለኢኮኖሚው የሚያበረክተው አስተዋፆ በጣም ከፍተኛ ሆኖ ሳለ ለዘርፉ የሚቀርበው ብድር አነስተኛ ነው ብለዋል፡፡ በመሆኑን ይህንን ችግር ለመፍታት በቀጣይ በግንባታው ዘርፍ ተወዳዳሪ እንዲሆን ከማድረግ አንፃር ከፍተኛ ሚና ይጫወታል የሚል እምነታቸውን ገልፀዋል ፡፡
በዘርፉ ተዋንያን መካከል ፍትሃዊ ውድድር መንፍስን መፍጠር ያስፈልጋል ያሉት ኢንጂነር ወንድሙ ፣ አሁን ላይ ሁሉም የዘርፍ አንቀሳቃሾች እኩል የሚወዳደርበት ሜዳ አልተፈጠረም ብለዋል፡፡ ይህንን ችግር በመቅረፍ ሁሉም እኩል ተጠቃሚ የሚሆንበት አካባቢ መፍጠር እንደሚያስፈልግ ጠቅሰዋል፡፡

ይህንን ኢፍትሃዊነት ማረጋገጥ የሚቻለው ደግሞ ዘርፉን ዲጂታይዝ በማድረግ ፣ በቴክኖሎጅ የታገዘ መረጃ መሰብሰብ መተንተን በቀጣይ ልንሰራቸው ላሰብናቸው ስራዎች ሰፊ ትኩረት ሰጥቶ ሚንስትር መስሪያ ቤታቸው እንደሚሰራ አረጋግጠዋል፡፡

የኢትዮጵያ የኮንስትራክሽን ስራ ተቋራጮች ማህበር ፕሬዝዳንት ኢንጅነር ግርማ ሃብተማርያም በበኩላቸው ያለፉት አመታት የኮንስትራክሽን ስራ ተቀራጮች ዘርፈ ብዙ በሆኑ ችግሮች እየተፈተነ መሆኑን ገልፀዋል ፡፡ ለችግሩ የውስጥና ዓለም አቀፋዊ ተፅዕኖዎች የራሳቸው ድርሻ አላቸው ያሉት ኢንጅነር የግንባታ ግብዓቶች ዋጋ መናር ፣ የግብይት ስርዓቱ ፈታኝ መሆን ፣ በዘርፉ የሚሰሩ ሰዎች ስራ አጥ መሆን እና የዘርፉን ህልውና ፈተና ውስጥ መውደቅ አንዱ ነው ብለዋል፡፡

የስራ ተቋራጮች ለሰሯቸው ስራዎች ወቅቱን ጠብቆ ክፍያ አለመክፈል በገንዘብ ፍሰት ላይ እያስከተለ ያለው ጫና ፣ የግንባታ አገልግሎት ግዥ በፍታሃዊነት ያለመመራት ሌላኛው የዘርፉ ችግር መኖሩን አንስተዋል፡፡ይህም የግንባታ ስራዎች በጥቂት ስራ ተቋራጮች ላይ ብቻ የመያዝና ብዙሃኑን ከስራ ውጭ የማድረግ አደጋዎች የሚጠቀሱ መሆናቸውን ተናግረዋል፡፡

በመሆኑም እነዚህን ፈተናዎች ለመቋቋም ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ማህበራቸው እየሰራ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

በኢግዚቢሽኑ ላይ ሲሳተፉ ያገኘናቸው የተለያዩ የግንባታ ግብዓት አቅራቢዎች እና አስመጭዎች በበኩላቸው ኢግዚቢሽኑ ምርትና አገልግሎቶቻቸውን ከማስተዋወቅ በዘለለ አምራችን ወይንም ግብዓት አቅራቢን ከዘርፉ አንቀሳቃሾች ጋር በቀጥታ የሚያገናኝ ነው ብለዋል ፡፡

## ‘አስታዋሽ ያጣው’ የጣፋጭ ምግቦች ዘርፍ



**በይድነቃቸው ዓለማየሁ**

የጣፋጭ ምግቦች ማለት በአብዛኛው ለምርታቸው ግብዓት ስኳርን የሚጠቀሙ እና በአብዛኛው ለቀን ውሎ እና ለበዓላት ፍጆታ የሚውሉ ናቸው፡፡ አንደ ከረሜላ፤ማስቲካ፤ቼኮሌቶች፤ኬኮች፤ብስኩቶች፤ ጣፋጭ ቁርሶች፤ ከለውዝ የሚሰሩ ጣፋጭ ምግቦችን እና የታሸጉ ምግቦች ይገኙበታል፡፡
በዓለም አቀፍ ደረጃ ስለ ጣፋጭ ምግቦች ዘርፍ በወፍ በረር ስንመለከት ባለፈው የፈረንጆች አመት አሜሪካ እና ጃፓን የጣፋጭ ምግቦችን አምርቶ ለውጪ ገበያ በማቅረብ ተወዳዳሪ አልበረታቸውም፡፡ በዚያው አመት አሜሪካ 290 ቢሊየን ዶላር ገደማ ስታገኝ ጃፓን ደግሞ ወደ 250 ቢሊየን ዶላር አግኝታለች፡፡

በዘርፉ የተሰሩ ጥናቶች እንደሚጠቁሙት የጣፋጭ ምግቦች በአለምአቀፍ ገበያ ከአመት ወደ አመት ፍላጎቱ እየጨመረ የሚሄድ ሲሆን ገበያው በአማካይ በ1/3ኛ ያህል ዕድገት አለው፡፡ የሸማቹ ቁጥር ደግሞ በሚቀጥሉት 3 አመታት ውስጥ ወደ 7 ሚሊየን ሕዝብ ይደርሳል ሲሉ

ወደ ገጽ 10 የዞረ

# ውጤታማና ቀልጣፋ የሰው ሀይል ላይ ኢንቨስት በማድረግ የኢንዱስትሪ እድገትን የማፋጠን አስፈላጊነት



በአሸናፊ ምትኩ

በቅርቡ የተደረገው የተባበሩት መንግስታት ጉባኤ የተባበሩት መንግስታት የአፈሪቃ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን ተጠባባቂ ዋና ስራ አስፈጻሚ አንቶንዮ ፔድሮ የአፈሪቃ ሀገራት መሪዎችን በኢንዱስትሪ ክህሎት ላይ መዋለ ንዋያቸውን በማፍሰስ በአአፈሪቃ የኢንዱስትሪ ሽግግር እውን እንዲሆን ጥሪ አቅርበዋል።

በ78ኛው የተባበሩት መንግስታት ጉባኤ ላይ ከአንድ ወር በፊት ንግግር አድርገው ነበር። በዚህ ንግግራቸው አንቶንዮ ፔድሮ በአፍሪቃ አህጉር በስፋት የሚስተዋለውን የኢንዱስትሪ ክህሎት እጥረት እና የሙያ ብቃት የዘላቂ የዘላቂ ልማት ግቦችን ለማሳካት ከፍተኛ ተግዳሮት እንዲሆኑ አስጠንቅቀዋል።

አሁንበአፍሪቃያለውንየሙያክህሎት ችግር ለመፍታት ትምህርት ላይ መዋለንዋይ ማፍሰስን እንደሚጠይቅ የተናገሩ ሲሆን በተለይም በሙያና ቴክኒክ ትምህርትና ስልጠና ላይ በማተኮር ፍላጎትን መሰረት ያደረጉ ስልጠናዎችን በስፋት በመስጠት በአህጉሪቱ ያለውን እምቅ ሀብት ለሰው ልጆች እድገት መጠቀም ይገባል ብለዋል።

የዘላቂ ልማት ግብ 9 የሆነውና በኢንዱትሪ ፤ፈጠራና መሰረተ ልማት ላይ የተሰጠው ትኩረት በአግባቡ የሚተረጎም ከሆነ የ2030 የዘላቂ ልማት ግቦችን እና የ2063 የአፈሪቃ ህብረት አጀንዳ ማሳካት እንደሚቻል ተናግረዋል። የአፈሪቃ የኢንዱስትሪ ክህሎት ልማት ላይ ትኩረቱን ያደረገው የፓናል ውይይት በአፈሪቃ ህብረት በዩኒዶና በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ኢኮኖሚክ ኮሚሽን ጥምረት የተካሄደ ነው።

በአፍሪቃ ኢንዱስትሪ እድገት ዙርያ ትኩረቱን ያደረገው ውይይት አፍሪቃውያን በኢንዱስትሪ ዙርያ ያላቸውን ሀሳብ የሚለዋወጡበት መድረክ ሲሆን በተለይም የአፈሪቃን ኢንዱስትሪ ክህሎት ለማሳደግ እና የአምራች ዘርፉን ለማነቃቃት የአመራረት ስልቶች እሴትን እንዲጨምሩ ማድረግ ላይ ትኩረቱን ያደረገ ነበር።ከዚህም ባለፈ ተወያዮች በአፍሪቃ በስፋት የሚስተዋለውን የባለሙያ ፍልሰት ለማስቆም አለምአቀፍ የሰራተኛ ህጋጋትን ተግባራዊ ማድረግ ጠቃሚ እንደሆነ በመድረኩ ተገልጻል።

በአፈሪቃ የሚስተዋለውን የሙያ ክህሎት ክፍተት ማወቅና ምላሽ መስጠት አስፈላጊነት፡-

ምንም እንካን የሙያ ክህሎት ክፍተት በአፍሪቃ በስፋት የሚታወቅ ቢሆንም በዚህ ርእሰ ጉዳይ ያለው የተጠናከረ መረጃ ወይም ዳታ ውስንነት አለበት ብለዋል። አንቶንዮ ፔድሮ ስለሆነም እንዲህ አይነት ተግዳሮቶችን ለመቅረፍ የሚያስችል የሙያ ክህሎት ክፍተት ምርምርን ማካሄድ በሀገርአቀፍ ደረጃና በዘርፍ ማካሄድ አስፈላጊ ነው ብለዋል።

በሙያና ቴክኒክ ትምህርትና ስልጠና የሚደረገው የገንዘብ ድጋፍ አነስተኛ መሆን በኢንዱስትሪ የሰለጠነ የሰው ሀይል ለማፍራት የሚረገውን ጥረት አስቸጋሪ የሚያደርገው ሲሆን ይህንን ችግር ለመቅረፍ መንግስታት፤ የንግዱ ማህበረሰብና የትምህርት ተቃማት የጋራ የምክክር መድረክ በማድረግ የተሻለ የሀብት አመዳደብ እንዲኖርና በአፍሪቃ የተሻለ ክህሎት ልማት እውን እንዲሆን ያግዛል።

እንደ ፔድሮ አነጋገር አፍሪቃ አሁን ያለውን ተነሳሽነት ከፍ በማድረግ በአህጉሪቱ ወቅታዊ የሙያ ስልጠና እውን እንዲሆን ያስፈልጋል ብለዋል። ለአብነትም ያክል የአፍሪቃ ህብረት ኮሚሽን ከጆሀንስበርግ ዩኒቨርሲቲ ጋር የ5 አመት የትብብር ስምምነትን በመፈረም በሁለተኛ ዲግሪ የኢንዱስትሪ ፖሊሲ ፕሮግራም እንዲጀምር ተደርጋል። ይህ የትምህርት ዘርፍ የአፍሪቃ መንግስታት ምቹ የሆኑ የኢንዱስትሪ ፖሊሲዎች እንዲተገብሩ እና የረጅም ጊዜ የብሄራዊ ልማት ፖሊሲዎች እውን እንዲሆኑ ያደርጋል።

በአህጉሪቱ አስተማማኝ የሙያ ክህሎት እንዲያድግ ለትምህርት የሚመደበውን በጀት ምደባን ማሻሻል በተለይም ለቴክኒክ ስልጠና ልዩ ትኩረት መስጠት እና አመቺ የፖሊሲ ከባቢ ሁኔታ መኖሩን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። የቴክኒክ ድጋፍን በማመቻቸት የኢንዱስትሪ ክህሎት በቀላሉ በተለያዩ ፕሮጀክቶች ተግባራዊ እንዲደረግ እና አዳዲስ ቢዝነሶች እውን እንዲሆኑ ያግዛል። የአፍሪቃ ሀገራት ወሳኝ የሆኑ ክህሎቶችን ቁልፍ ለሆኑ የስራ ዘርፎች በማዳረስ እና ተጨባጭ የሆኑ የትግበራ እርምጃዎችን መውሰድ አለባቸው። አንድ ሀገር እድገት የሚለካው ውጤታማ ውጤታማ በሆነ የሰለጠነ የሰው ሀይል በመሆኑ የአፍሪቃ ህብረት በአህጉሪቱ ያለውን እምቅ ችሎታ እና የስራ ፈጠራ ክህሎትን በመጨመር ወደ መደበኛው ኢኮኖሚ እንዲካተቱ ማድረግ ያስፈልጋል።

በመተሳሳይ መልኩ ሀገራት ዜጎችን የማብቃት፤የማሰልጠን እና የቴክኒክ ድጋፍ በማድረግ በኢ መደበኛ ያሉ የስራ መስኮችን አቅም በማሳደግ ለመደበኛው ኢኮኖሚ የተሻለ ክህሎት ያለው ዜጋ እንዲያበረክቱ መስራት አስፈላጊ ነው።

# የአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማህበራት ም/ቤት ሠራተኞች ምርታማነትን ለማሳደግ ተግተው እንዲሰሩ የምክር ቤቱ ከፍተኛ ሀላፊዎች ጥሪ አቀረቡ።



በስታፍ ሪፖርተር

የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት በኢትዮጵያ ንግድና ኢንቨስትመንት እንዲፋፋ ከሚሰሩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች መካከል አንዱና ግንባር ቀደም ነው። በአሁኑ ወቅት ከ70 በላይ ሰራተኞችን በቋሚነት በመቅጠር ቀልጣፋ አገልግሎትን እየሰጠ የሚገኝ ተቋም ሲሆን የንግዱ ማህበረሰብ ድምጽ እንዲሰማ ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል። ለዚህም ስኬት የተቋሙ ሰራተኞችና አመራሮች ያበረከቱት አስተዋጾ ከፍተኛ እንደሆነ በድርጅቱ አመታዊ የሰራተኞች ቀን አከባበር ላይ ተገልጿል።

“በአንድ ድርጅት ውስጥ አወንታዊ የሥራ ባህልን ለማዳበር እና የላቀ ብቃትን ለማነሳሳት ዕውቅና መስጠት ወሳኝ ሚና ይጫወታል። በተጠናቀቀው በጀት ዓመት በተለያዩ የሥራ ክፍሎች ሠራተኞቻችን ላደረጉት የላቀ አስተዋፅኦ ዕውቅና የምንሰጥበት እና የምናደንቅበት ብቻ ሳይሆን ይህ ሥነ-ስርዓት አንድ ላይ እንድንሰባሰብ እና እያንዳንዱ ግለሰብ ያሳየውን ችሎታ፣ የሥራ ተነሳሽነት፣ ቁርጠኝነት እና ጥረት በጋራ ዕውቅና የምንሰጥበትም ነው በማለት የምክር ቤቱ ዋና ጸሀፊ አቶ ሺበሺ ቤተማርያም በእለቱ ባደረጉት ንግግር ገልጸዋል።

**“የማንኛውም የተሳካ ድርጅት ልብ የሚገኘው በሠራተኛው ውስጥ ነው”** ያሉት ዋና ጸሀፊው በተቋም ውስጥ የሚገኙ ሰራተኞችን እውቅና መስጠት የድርጅቶች እቅድና ግብ እንዲሳካ የበኩሉን አስተዋጾ እንደሚያደርግ አክለው የተናገሩ ሲሆን በወቅቱ እውቅና የተቸራቸው ሰራተኞች የተቋሙን ግቦች በማሳካት፤ ተግዳሮቶችን በመጋፈጥ እና ውጤቶችን በማስመዝገብ አዳዲስ ሀሳቦችን በመቅረጽና በመተግበር ለጋራ ግቦቻ ስኬት ያበረከቱትን አስተዋጾ አድንቀዋል።

በዚህ የእውቅና ስነስርአት ላይ ንግግር ያደረጉት የምክር ቤቱ ፕረዚደንት ወ/ሮ መሰንበት ሸንቁጤ ምክር ቤቱ በጠንካራ አመራር በመታገዝ ላለፉት በርካታ ወራት የንግዱን ማህበረሰብ ድምጽ ሊያሰሙ የሚችሉ በርካታ ስራዎችን መስራቱን የገለጹ ሲሆን ለዚህም የምክር ቤቱን ከፍተኛ አመራሮችና ሰራተኞች ያበረከቱትን አስተዋጾ አድንቀዋል። አመታዊ የሰራተኞች ቀንን ማክበር በርካታ ጥቅሞች እንዳሉት የተናገሩ ሲሆን አንድ ተቋም ለሰራተኞቹ እውቅና በሰጠ ቁጥር ውጤታማ የመሆን እድሉ ከፍ ይላል ብለዋል ፕረዚደንቷ።

# ብሪክስ እና የኢትዮጵያ የግሉ የምጣኔ ሀብት ዘርፍ




የየአባል አገሮችን የመጀመሪያ ፊደላት በመደርደር BRICS (ብራዚል፣ ሩሲያ፣ ህንድ፣ ቻይና እና ደቡብ አፍሪካ) ተብሎ የሚታወቀዉ ጥምረት ምንድን ነው? አሁን ኢትዮጵያን ጨምሮ ስድስት አገራትን በማስገባት አድማሱን እያሰፋ ነው:: አጠቃላይ የእስካሁኑን BRICS ለመረዳት ቢያንስ አምስት መለያ መገለጫዎች እንዳሉት አይተን እንጀምር:: አንደኛ አባል አገራቱ በዓለም ላይ በፍጥነት እያደጉ ካሉ ምጣኔ ሀብቶች ግንባር ቀደሞች ናቸው:: ይህም ለብዙ ተከታታይ ዐመታት የተመዘገበ ነው:: ሁለተኛ፣ አሁን በዓለም ላይ ያሉ ገዢ አሳቦችና ተቋማት አካታችነትና ሚዛናዊነት ይጎድላቸዋል ብለው የሚያስቡ ናቸው( የፀጥታዉ ምክርቤት፣ የዓለም የገንዘብ ተቋም፣ የዓለም ባንክ):: ሦስተኛ አገራት የፖለቲካም ይሁን የባህል ሉዐላዊነታቸው በማንም የዉጭ አካል ግፊት እንዲቀየር መደረግ የለበትም ብለው የሚያምኑ ናቸው:: አራተኛ ከዶላር ተጽእኖ ለመላቀቅና ቢቻል ሌላ አዲስ መገበያያ ገንዘብ መጠቀም መጀመር፣ ባይሆን ግን አባላቱ የሁለትዮሽ ንግድ ሲያካሂዱ በየራሳቸው ገንዘብ ለመገበያየት መሻት :: አምስተኛ አባል አገራቱ BRICS አሁን ያለዉን ሚዛን ካየን በምጣኔሀብት የዓለምን ሲሶ አጠቃላይ አገራዊት ምርት ይቆጣጠራል/ GDP::የዓለም ግማሹ ህዝብ አካባቢ(46%) የማህበሩ አባል በሆኑ አገሮች ይኖራል:: ነዳጅ እና ጋዝ ፣የመኪና ምርት፣ የግብርና ምርት እና እጅግ ተፈላጊ ማእድናት ያሏቸው አገሮች ናቸው:: ስንዴ፣ ቡና፣ ሸንኮራ፣ ስኳር እና የመሳሰሉ የግብርና ዉጤቶች በሩስያ፣ በብራዚል በህንድ በኢትዮጵያ ጭምር ሰፊ አቅም አላቸው:: በሳይንስ፣ በቴክኖሎጂ እና በኢንደስትሪ ምርት እየገሰገሱ ስለሆነ፣ በአባል አገራቱ የሚገኙ ነጋዴዎች፣ መዋለ ንዋይ አፍሳሾች፣ የቴክኖሎጂ ፈጠራ ላይ የተሠማሩ ድርጅቶች የሰፋ ገበያ ለማግኘት ስለሚችሉ ታላቅ እድል ነው ለማለት ይቻላል:: ይሁንና እድል በተጠቃሚዉ ቁርጠኝነትና ዝግጅት የሚወሰን ስለሆነ፣ አባል መሆን ብቻዉን የሚያመጣዉ ጥቅም የለም:: እንዲያዉም ላቅ ያሉ ተወዳዳሪዎች ወደ ገበያዉ ስለሚቀላቀሉ ፣ የገበያ ድርሻን የማጣት ፈተና ዉስጥ ሊገቡ ይችላሉ::

የBRICS አባል ስንሆን ፣ በኢትዮጵያ ያለው የግል ዘርፍ፣ አሠራሩን ካዘመነ እና የምርቱን ጥራት ላቅ ካደረገ፣የሚከተሉትን ትሩፋቶች ሊያገኝ ይችላል:: የገበያ ተደራሽነት፦ የ BRICS አባል አገሮች በዓለም አቀፍ ደረጃ በምጣኔ ሀብት እየፈረጠሙ ያሉ እና ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ያላቸው፣ የወጪና ገቢ ንግዳቸው ባያሌው እየሰፋ ያለ፣ ያገር ዉስጥ ገበያቸውም ከፍተኛ ስፋት ያላቸው ናቸው:: በአባል ሀገራት ያሉ የግል ንግድ ድርጅቶች የደንበኞቻቸውን መሠረት ለማስፋት እና ትርፋማነታቸውን ለማሳደግ ይህንን ተደራሽነት መጠቀም ይችላሉ:: አገራቱ ታሪፍ ለመቀነስ፣ የጉምሩክ ኮታ ለማንሳት እና በትብብር ለመሥራት ህልም ስላላቸው፣ በየአባል አገራት የሚገኙ ኩባንያዎች በቀላሉ ምርትና አገልግሎት ካንዱ ወዳንዱ በማንቀሳቀስ ትርፋማ ለመሆን እና ለማደግ ይችላሉ::
የኢንቨስትመንት እድሎች፦የ BRICS አባል አገሮች በተለያዩ ዘርፎች አዋጭ የመዋእለ ንዋይ/ኢንቨስትመንት እድሎችን ይሰጣሉ::ለምሳሌ የቻይና ኩባንያዎች ኢትዮጵያ ገብተው ሀብታቸዉን ፈሰስ ያደርጋሉ:: ይህ በፊትም ያለ ቢሆንም ፣ BRICS እየጠነከረና ስምምነቶች እየሰፉ ሲሄዱ በመጠን ስለሚጨምር፣ የኢትዮጵያ ኩባንያዎች በሽርክና ወይም በግባት አቅራቢነት ወይም በመጨረሻ ምርት ደምበኝነት እድሉን ለመጠቀም ይችላሉ:: ከዚህ በተጨማሪም ጠንከር ጠንከር ያሉ የኢትዮጵያ የንግድ ድርጅቶች በሌሎች አባል አገራት ገበያ በአምራችነትና እና በነጋዴነት ሊሳተፉ ይችላሉ ላቅ ባለ ደረጃ:: በሌላ አገላለጽ የግል ንግድ ድርጅቶች ከውጪ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት (FDI) ተጠቃሚ መሆን እና በጋራ የንግድ ሥራዎች ላይ መሳተፍ እና ትርፋማነታቸዉን ሊያሳድጉ ይችላሉ::የየአባል አገራት መንግስታትም ለውጭ ባለሀብቶች ማበረታቻዎችን ለምሳሌ የታክስ እፎይታ ወይም የተስተካከሉ ደንቦችን፣ የቀረጥ እና ፍተሻ ደረጃዎችን ሊያሻሽሉላቸው ስለሚችሉ የንግድ ሥራ እንቅፋቶች እየቀነሱ ይሄዳሉ ተብሎ ይጠበቃል::

በሳይንስና ቴክኖሎጂ ለማደግ፦ ከላይ እንደተጠቀሰው፣ የ BRICS አባል አገሮች በቴክኖሎጂ ፈጠራ ግንባር ቀደም ናቸው( ቻይና በኤሌክትሪክና ማንኛዉም ማሺነሪ፣ ሩሲያ በወታደራዊ እና በሳይበር፣ ህንድ በሶፍትዌር):: የግል ንግድ ድርጅቶች የላቁ ቴክኖሎጂዎችን ለማግኘት ከሀገር ውስጥ ኩባንያዎች ጋር መተባበር፣ ተወዳዳሪነትን ማጎልበት እና የቆየዉን አሠራራቸዉን ለማዘመን ፣ ያልተለመዱ ምርቶችንም ለማስተዋወቅ ይችላሉ:: ቴክኖሎጂን በቀላሉ ከወዳጅ አገራት ማግኘት፣ ምርትን በአጭር ጊዜ፣ አነስ ባለ ወጪ እና በላቀ ጥራት በማምረት፣ በየትኛዉም ገበያ ደረታቸዉን ነፍተዉ ሊወዳደሩ ያስችላቸዋል:: የእውቀት ልውውጥ ፕሮግራሞች እና የምርምር ትብብር እርስ በርስ የቴክኖሎጂ ሽግግርን ሊያሳልጡ ይችላሉ::

ታዲያ ለኢትዮጵያ የግሉ ዘርፍ ግልጽ መሆን ያለበት ነገር ፣ እነዚህ ከላይ የጠቀስናቸው ትሩፋቶች፣ እንዲሁ የሚመጡ ሳይሆኑ ከጎናቸው ትላልቅ ፈተናዎች አሉ:: እንደ ቻይና ያሉ አገሮች ዉስጥ ያሉ ድርጅቶች በቴክኖሎጂ የፈረጠሙ በብዛት የሚያመርቱ እና በዝቅተኛ ዋጋ ወደ ገበያ ምርት የሚያቀርቡ በመሆናቸው፣ BRICS ሊያመጣቸው የሚችሉ እድሎችን ሁሉ አሟጠዉ ሊወስዷቸው ስለሚችሉ ሱሪን ጠበቅ አድርጎ መሥራት፣ አርቆ ማቀድና እና በትጋት መገዳደር ያስፈልጋል:: BRICS ይዟቸው የሚመጣቸውን በረከቶች በምላት እንዳንጠቀም ፣ እንቅፋት ሊሆኑ የሚችሉ ጉዳዮች ለመጥቀስ ያክል የባህልና አሠራር ልዩነቶች፦ በ BRICS አገሮች ውስጥ የንግድ ሥራ መሥራት የባህል ልዩነቶችን እና በየአካባቢ ያሉ የንግድ ልማዶችን መረዳትን ይጠይቃል:: የግል ዘርፍ ፣ በሌሎች ገበያዎች ጠንካራ ግንኙነቶችን ለመገንባት እና አመኔታን ለማግኘት የተለያዩ ስልቶችን ለመጠቀም ይችላሉ:: ለምሳሌ የኢትዮጵያ ድርጅቶች ህንድ ሂደው ሲሠሩ የህንድን ገበያ የሚያዉቁ የአካባቢዉን ተወላጆች መቅጠር፣ የየአገሩን የንግድ ህግ የሚያዉቁ እና የሚያማክሩ ድርጅቶችን መቅረብ እና በመንግሥት ደረጃ ጥናት እየተሠራ እንዲነገራቸው ማድረግን ሊጨምር ይችላል:: በዚህ መልክ የባህል ክፍተት የሚፈጠረዉን የንግድ ሥራ እንቅፋት ለመቅረፍ ወይም ለመቀነስ ይቻላል::

በሁለተኛ ደረጃ ዉስብስብ የንግድ ደንቦች እና አሠራሮች፦ በተራ ቁጥር አንድ ያየነው በዋናነት ከባህሉ የሚመንጨዉን ነው:: ልክ እንደነሱ ሁሉ፣ እያንዳንዱ BRICS አገር የራሱ የሆነ ልዩ የንግድ እና ኢንቨስትመንት የቁጥጥር ማዕቀፍ አለው፣ይህም ለውጭ አገር ድርጅቶች

ወደ ገጽ 8 የዞረ

# ብሪክስ እና የኢትዮጵያ የግሉ የምጣኔ ሀብት ዘርፍ

ከ ገጽ 7 የዞረ

አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል:: የግሉ ዘርፍ ድርጅቶች፣ ከሌላዉ አገር የጥራት፣ የቀረጥ እና ሌሎችም መስፈርቶችን ተገዢነትን በማረጋገጥ ኢንቨስት ማድረግ አለባቸው:: ለዚህ መፍትሔው የህግ ምክር መፈለግ እና ከሀገር ውስጥ የኢንዱስትሪ ማህበራት ጋር መሳተፍ የጋራ መግባባት እንዲኖር ፣ ችግሮች ሲፍጠሩም በፍጠንት የሚፈቱባቸው መላዎችን መዘየድ ይገባል::

የመሰረተ ልማት ዝርጋታ: ምንም እንኳን በየአባል አገራቱ በተለይ በቻይና ጉልህ የመሠረተ ልማት ዝርጋታ እመርታ ቢታይም እስካሁን ድረስ በአንዳንድ የBRICS ሃገራት የመሰረተ ልማት ክፍተቶች አሉ:: የግሉ ዘርፍ እነዚህን የመሠረተ ልማት ውስንነቶች እንደ ገበያ እድል ተጠቅሞ ኢንቨስት ሊያደርጋብቸው ይችላል:: ወይም እንደ እንቅፋት አይቶ ወደ ሌላ ገብያ ሊያመራ ይችላል:: ከአካባቢው መንግስታት እና መሠረተ ልማት ገንቢዎች ጋር መተባበር የጋራ ተጠቃሚነትን ወደ ሚያረጋግጥ አጋርነት ሊያመራ ይችላል::

የኢትዮጵያ የግሉ ዘርፍ ከBRICS ለመጠቀም እና ተግዳሮቶችን ለማስወገድ እንዲችል ምንምን እርምጃዎች ያስፈልጋሉ?

የገበያ ጥናት:- የኢትዮጵያ የግል ዘርፉም ሆነ ተያያዥነት ያላቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ፣ በBRICS አገሮች ውስጥ ሊኖሩ የሚችሉ እድሎችን ለመለየት ሰፊ የገበያ ጥናት ማድረግ አለባቸው:: ይህ የሸማቾች ምርጫዎችን፣ የገበያ አዝማሚያዎችን እና ውድድርን እንዲረዱ ይረዳቸዋል::የገበያ ጥናትና ምርምር ድርጅቶችን በመቅጠር ጥናት በማሠራት ወይም ከሌላ አገር የንግድ ድርጅቶች ጋር መረጃ በመለዋወጥ ሊከናወን የሚችል ነው::

የንግድ ሰዎች የሌላ ገር እንዲጎበኙ ወይም አዉደ ርእዮች እንዲዘጋጁ ማድረግ:- በBRICS አባል ሀገራት በሚዘጋጁ የንግድ ጉብኝቶችን እና አዉደ ርእዮች ላይ መሳተፍ የኢትዮጵያ ንግድ ድርጅት ደንበኞችን፣ አጋር ድርጅቶችን እና ባለሀብቶችን በቀጥታ እንዲያገኙ ያስችላል::

የአቅም ግንባታ: ሌላው እርምጃ የኢትዮጵያ ንግድ ድርጅቶች ከBRICS ገበያዎች ጋር በብቃት ለመስማራት አስፈላጊውን ክህሎትና እውቀት በማዳበር ላይ ማተኮር አለባቸው:: ይህ በስልጠና መርሃ ግብሮች፣በተግባር ተኮር ስልጠናዎች እና የእውቀት መጋራት መድረኮች ሊገኝ ይችላል:: ከዩኒቨርሲቲዎች ወይም ከኢንዱስትሪ ማህበራት ጋር የታለሙ የሥልጠና መርሀ ግብሮችን በመንደፍ መተገበርም ይቻላል::

ትስስርና እና ሽርክና መፍጠር: በBRICS አገሮች ውስጥ ጠንካራ ትስስርና አጋርነት መገንባት ለኢትዮጵያ ንግድ ድርጅቶች ወሳኝ ነው:: ከአገር ውስጥ ንግድ ምክር ቤቶች፣ ከኢንዱስትሪ ማኅበራት እና ከሠራተኛ ማኅበራት ጋር መቀራረብ ትርጉም ያለው ግንኙነት እንዲኖር ያስችላል:: ከዋና ዋና ባለድርሻ አካላት ጋር ግንኙነት ለመፍጠር በንግድ ኮንፈረንስ እና ዝግጅቶች ላይ የነቃ ተስትፎ በማድረግ ፣ የሚፈልጉትን ወይም የሚያቀርቡትን ምርትና አገልግሎት መሰረት አድርጎ መዋዋል፣ የመግባቢያ ሰነድ መፈራረም ወዘተ መሥራት ይቻላል::

በአገር ደረጃ የግል ንግድ ድርጂቶን ከ BRICS ጋር በተያያዘ የሚያጋዝ መድረክ መፍጠር: የኢትዮጵያ ንግድ ድርጅቶችየ BRICS ገበያዎችን ለማግኘት ከመንግስት በንቃት ድጋፍ መጠየቅ አለባቸው:: የመንግስት ኤጀንሲዎች ጠቃሚ ግብአቶችን፣ መረጃዎችን እና የዲፕሎማሲያዊ ዕርዳታዎችን ሊሰጡ ይችላሉ:: ከንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ወይም ከሚመለከታቸው የንግድ ማስፋፊያ ኤጀንሲዎች ጋር በቅርበት በመሥራት ላገር የሚጥቅሙ ሥራዎችን ለመሥራት ይቻላል:: የንግድ ድርጅቶችን ይበልጥ ትርፋማ በማድረግ( የሥራ እድል፣ የዉጭ ምንዛሪ ማመንጨት፣ ከዉጭ የሚመጣዉን እቃ በመተካት፣ ጥራት ባለው ምርት ያገርን ስም በማስመስገን)::

ለማጠቃለል ያህል፦የ BRICS ጥምረት በአባል አገሮች ውስጥ ላሉ የግል ንግድ ድርጅቶች ጉልህ ጥቅሞችን ይሰጣል::የተወሰኑትን ለመጥቀስ የገበያ ተደራሽነትን፣ የኢንቨስትመንት እድሎችን እና የቴክኖሎጂ እድገቶችን በመጠቀም የግል ንግዶች በእነዚህ ግሥጋሴ ላይ ባሉ ኢኮኖሚዎች ውስጥ አብረዉ ማደግ ይችላሉ:: ሆኖም፣ እንደ የባህል ልዩነቶች፣ የንግድ ደንብና አሠራር ውስብስብ ችግሮች እና የመሠረተ ልማት ውስንነቶች ያሉ ተግዳሮቶችን በደንብ ማጤን ያስፈልጋል:: የኢትዮጵያ ንግድ ድርጅቶች የBRICSን አቅም ለመጠቀም እና በዓለም ገበያ እድገታቸውን ለማስፋት የገበያ ጥናትን፣ የአቅም ግንባታ እና ትስስርን ጨምሮ የተጠኑ እርምጃዎችን መውሰድ አለባቸው::





# Have you registered

**for the upcoming 14th Addis Chamber International Agriculture and Food Trade fair/ AgriFex/ 2023 at the Millenium Hall, Addis Ababa?**

REGISTER NOW



## 'አስታዋሽ ያጣው' የጣፋጭ ምግቦች ዘርፍ

ይተነብያሉ::

ወደ አገራችን ስንመለስ በነገራችን ላይ በኢትዮጵያ የጣፋጭ ምግቦች ከግማሽ ምዕተ አመት በላይ ያስቆጠረ ታሪክ አለው ይባላል:: ነገር ግን ዘርፉ በሌላው የዓለም አገራት ከደረሰበት ደረጃ ሲታይ የተረሳ እስኪመስል ወደ ኋላ ቀርቷል ማለት ያስደፍራል:: በነገራችን ላይ በጣፋጭ ምግቦች ዘርፍ የተሰማሩ አገር በቀል ፋብሪካዎች ቁጥር 153 ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ ለውጪ ገበያ ማቅረብ የሚችሉት 12 ገደማ ይሆናል:: ለመሆኑ አገራችን የጣፋች አምራቾች ችግር ምን ይሆን ስንል ወደ ኢትዮጵያ የስኳርና ጣፋጭ ምግቦች ማሕበር ጎራ ብለን አንዱ ዘርፉን ቀፍድዶ የያዘው ዋናው ጉዳይ የስኳር ነገር መሆኑን ሰማን:: የማሕበሩ ሊ/መንበር አቶ ካሣሁን ገ/ጊዮርጊስ እንደሚሉት የስኳር እና የጣፋች ምግቦች አምራቾች እስከ ቅርብ አመታት በፊት ወርቃማ ወራትን አሳልፈዋል:: በተለይ ከቅርብ አመታት ወዲህ በአገር ደረጃ የተፈጠረው አና አሁንም ያልተፈታው የስኳር እጥረት ነው ይላሉ:: ብዙዎቹ አምራች ኢንዱስትሪዎች ከስረው ሠራተኛ አሰናብተው ዘግተዋል:: ሎሎቹ ደግሞ በውጪ ምንዛሬ የገቡ ማሽነሪዎች በዝገት እየተበሉ ከጥቅም ውጪ ሆነዋል :: ይህንን መንግሥት አይቶ አፋጣኝ መፍትሔ ካሰጠው ኢንዱስትሪዎቻችን ጥቂት ቆይተው መክሰማቸው አይቀርም ይላሉ::

የጣፋጭ ዘርፉ እንዲህ ባለ ሁኔታ ውስጥ እየተንገዳገደ ባለበት ችግሩን ብዙዎች ወደ መዘጋት ጎዳና ሲገቡ ሌሎቹ ደግሞ እስትንፋሳቸው አለ የሚባሉት አምራቾች ቁጥር ከአንድ እጅ ጣቶች ቁጥር ብዙም አይበልጥም:: በኢትዮጵያና በጎረቤት ሀገራት መካከል ያለውን ሁኔታ ለማነጻጸር ያክል በኬንያ ቁጥራቸው 32 ያህል ሲሆን በያዝነው የፈረንጆች አመት አመታዊ ሽያጫቸው ወደ 9 ቢሊየን ዶላር ይደርሳል ተብሎ ይጠበቃል:: ይህ ማለት የአገራችን የአንድ አመት ኤክስፖርት 3 እጥፍ መሆኑ ነው :: ይህንን ለማሳያ ከቅርቡ አነሳን አንጂ አገራችን ለጣፋጭ ምግቦች ምርትም ሆነ ግብዓት ለማምረት የበለጠ ተስማሚ ናት:: አሁን ላይ ቢያንስ ለውጪ ገበያ ምርታቸውን ማቅረብ የሚችሉ ተብለው ለተለዩት ጥቂት ፋብሪካዎች የመንግሥት ትኩረት ካገኙ ለአገራችን የውጪ ምንዛሬ እጥረት የበኩላቸውን ያስገኛሉ የሚል እምነት አለ:: መንግሥት ለማንዩፋክቸሪንግ ወይም አምራች ዘርፉ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ አንደሚንቀሳቀስ ይታወቃል::

በተለይ "ኢትዮጵያ ታምርት" በሚል መንግሥት የጀመረው ዘመቻ አዳዲስ ኢንዱስትሪዎችን አምራቹ ዘርፍ በተለይም ለጣፋጭ ኢንዱስትሪዎች ትሩፋት የሚያመጣ ይመስላል:: መንግሥት በኢትዮጵያ ታምርት በሚል የጀመረውን ጥረት ኢንዱስትሪዎችን ከማስፋፋት ሥራው ጎን ለጎን እየከሰሙ የሚሄዱትን አገር በቀል አምራቾች አንዲያገግሙ ጥረት ማድረግ አንዳለበት ይታመናል::

ይህ ማለት የጣፋጭ ዘርፉ አሁንም ቢሆን ሙሉ በሙሉ የጨለመ እና የተዘጋ ከባቢ ሁኔታ ውስጥ አይደሉም:: በአንድ በኩል የተስፋ ጭላንጭል በሌላ በኩል ደግሞ ስጋት አላቸው:: በተለይ የኮንትሮባንድ ችግር ፤የውጪ ምንዛሬ እና የስኳር እጥረት የመሳሰሉት ተግዳሮቶችን ማሸነፍ ከተቻለ አምራች ኢንዱስትሪዎቻችን የአገር ውስጥ ገበያን አልፈው ኤክስፖርት የማድረግ አቅሙና ዕድሉ አላቸው :: ነገር ግን ለዘርፉ መንግሥት አፋጣን ምላሽ እና የፖሊሲ ድጋፍ ዋናው ጉዳይ መሆኑ መዘንጋት የለበትም::


# አዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት

ADDIS ABABA CHAMBER OF COMMERCE AND SECTORIAL ASSOCIATIONS

አዲስ ቻምበር
ADDIS CHAMBER

የአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት/ አዲስ ቻምበር/ ለአባላቶቹ እና ለመላው የንግዱ ህብረተሰብ በዲጂታል የታገዘ የ2024-2025 እትም የቢዝነስ ዳይሬክተሪ/ የንግድ ማውጫ/ እነሆ እያዘጋጀ ይገኛል::

ይሄው በሞባይል እና በሌሎች የኤሌክትሮኒክስ መተግበሪያ ዘዴዎች የተዘጋጀው የንግድ ማውጫ ፤ ለነጋዴዎች፣ ለውጪ ባለሃብቶች፣ለስራ ፈጣሪዎች፣ለውጪ ሀገር ዲፕሎማቶችና ሚሲዮኖች ፈጣን የመረጃ ምንጭ ሆኖ ያገለግላል::

በየሁለት አመቱ ታትሞ በሚሰራጨው እትም ላይ የድርጅትዎን ምርትና አገልግሎት በሀገር ውስጥ እና በአለም ዙሪያ እንዲያስተዋውቁ አዲስ ቻምበር በአክብሮት ይጋብዛል::

የኩባንያዎትን የቢዝነስ መረጃ በንግድ ማውጫው ላይ በማስፈር በየትኛውም የአለም ገበያ ላይ ለሚሊዮኖች ተደራሽ ይሁኑ!!!

ይቻላል
It's Possible!

ንግድ ምክር ቤት ህንፃ ሚክሲኮ አደባባይ፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
Chamber of Commerce Building Mexico Sq. Addis Ababa, Ethiopia
ስልክ/Tel: +251 115 518055 ፋክስ/Fax: +251 115 511479
P.O.Box 2458 አዲስ አበባ፣ ኢትዩጵያ/Addis Ababa Ethiopia ኢ. ሜይል/E-mail: Infor@addischamber.com

# Addis Chamber Training Institute (ACTI)

## List of Upcoming Training Programs

| No. | Training Topic | Delivery Date | Time | Training Fee | | Venue | Remark |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | Member | Non-Member. | | |
| 1 | Advanced Customer Service | October 10 - 11, 2023 | 8:30AM - 5:30PM | 5,929 | 7,115 | Hotel | 2 full days |
| 2 | Cost Accounting | October 16 - 20, 2023 | 8:30AM - 12:30PM | 3,542 | 4,250 | ACTI | 5 half days |
| 3 | International Trade Service & Ethiopian Export/Import Practice | October 16 - 20, 2023 | 1:30PM - 5:30PM | 3,542 | 4,250 | ACTI | 5 half days |
| 4 | Strategic Planning and Management | October 17 - 19, 2023 | 8:30AM - 5:30PM | 8,591 | 10,309 | Hotel | 3 full days |
| 5 | Customer Relationship Management | October 17 - 19, 2023 | 8:30AM - 5:30PM | 8,591 | 10,309 | Hotel | 3 full days |
| 6 | International Financial reporting Standards | Oct. 23 – Nov. 10, 2023 | 8:30AM - 12:30PM | 3,542 | 4,250 | ACTI | 15 half days |
| 7 | Supplies and Materials Management | October 23 - 27, 2023 | 1:30PM - 5:30PM | 3,542 | 4,250 | ACTI | 5 half days |
| 8 | Tax Accounting, an Ethiopian Perspective | November 6-10, 2023 | 1:30PM - 5:30PM | 3,542 | 4,250 | ACTI | 5 half days |
| 9 | Knowledge Management | November 7-9, 2023 | 8:30AM - 5:30PM | 8,591 | 10,309 | Hotel | 3 full days |
| 10 | Financial/Capital Market and Security Analysis | November 7-10, 2023 | 8:30AM - 5:30PM | 11,858 | 14,230 | Hotel | 4 full days |
| 11 | Asset Valuation | November 13-24, 2023 | 8:30AM - 12:30PM | 6,383 | 7,659 | ACTI | 10 half days |
| 12 | Internal Audit | November 20-24, 2023 | 1:30PM - 5:30PM | 3,542 | 4,250 | ACTI | 5 half days |
| 13 | Decision Making and Problem Solving | November 21-22, 2023 | 8:30AM - 5:30PM | 5,929 | 7,115 | Hotel | 2 full days |
| 14 | Financial Management | Nov. 27-Dec. 1, 2023 | 8:30AM - 12:30PM | 3,542 | 4,250 | ACTI | 5 half days |
| 15 | Customs Procedure | Nov. 27-Dec. 1, 2023 | 1:30PM - 5:30PM | 3,542 | 4,250 | ACTI | 5 half days |
| 16 | Emotional Intelligence | November 28-29, 2023 | 8:30AM - 5:30PM | 5,929 | 7,115 | Hotel | 2 full days |
| 17 | Training of Trainers | November 28-30, 2023 | 8:30AM - 5:30PM | 8,591 | 10,309 | Hotel | 3 full days |

**For further information, please contact the Training Institute through 011-551-3882, 011-551-8055 ext. 229, 0911194965, 0911343078, dejedesalegn@gmail.com and hiwottlhn9@gmail.com**

አዲስ ቻምበር
ADDIS CHAMBER